Fundraising speech May18, 2019

ከቡራትና ከቡራን እንደምን አመሻችሁ።

«ኅብረታችን የጥንካሬያችን መሠረት ነው።»

በምሽቱ ፕሮግራም እንደምትደሰቱ ሙሉ ዕምነቴ ነው።

በዛሬው ምሽት እዚህ ቦታ ተገናኝተን ለማኅበራችን የገንዘብ ማሰባሰቢያ ይሆን ዘንድ በተዘጋጀው የእራትና መዝናኛ ፕሮግራም ላይ መልካም ፈቃዳችሁ በመሆኑና በመገኘታችሁ በማኅበሩ በቦርዱና በራሴም ስም ሁላችሁንም እጅግ በጣም ላመሰግን እወዳለሁ።

በየዓመቱ በምናደርገው በዚህና ሌሎችም ዝግጅቶች በመተባበር የገንዘብና የጥሬ ዕቃ አስተዋጽኦና ዕርዳታ ላደረጋችሁልን የንግድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ከልብ የመነጨ ምስጋናችን እጅግ ከፍ ያለ ይሆናል። ለወደፊቱም ቢሆን ይህ ዓይነቱ ትብብርና ተሳትፎ ለሁልጊዜውም እንደማይለየን የማኅበሩ አመራር ቦርድ ሙሉ ተስፋ ያደርጋል።

ከዚህም አያይዤ ላሳስባችሁ የምወደው በአሁኑ ወቅት እዚህ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ተጠሪና መመኪያ ሊሆን የሚገባው የኢትዮጵያ ማኅበር በቶሮንቶና አካባቢው ከምንጊዜውም የበለጠ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ። ይህም በመሆኑ ምክንያት ሁላችሁንም የማሳስበው ዛሬ ይህን ማኅበር ሁላችንም ተባብረን በእንክብካቤ ካልያዝነው በስተቀር በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ ውድቀት እንደሚያመራ ተገንዝበን ይልቅዬ ሁላችንም ማኅበሩን ካለበት ችግር ለማላቀቅ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

የሕዝብ አገልግሎት ሊሰጥ የተሰለፈ ማኅበር አባላቱ በሚፈልጉት መጠን አገልግሎት መስጠት ካልቻለ አቅሙ እየተዳከመ ይሄድና በመጨረሻም ሕልውናው እሚገታበት ወቅት እሩቅ እንደማይሆን ለሁላችንም ግልጽ ሊሆንልን ይገባል።

ለማንኛውም መልሱ አጭር ነው። ዋነኛው መፍትሄ መተባበር ይመስለኛል። እያንዳዳችን አብዛኛው ትኩረታችን የግል ሕይወታችን ላይ መሆን አለበት ብለን ብናስብም በሌላ በኩል ደግሞ የጋራ የሆነ ጥቅማችንንና መብታችንን ማስከበር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ከመስጠትም በላይ ተግተን መሥራት እንዳለብን በጣሙን ላሳስብ እወዳለሁ። በጊዜው እኛ ባለንበት ሁኔታ ደስ ብሎን ኑሯችን የተሟላ ቢመስለንም መብታችን ካልተከበረ ግን የተሟላ ሁኔታ ተፈጥሯል ለማለት እንደማይቻል ግልጽ ይመስለኛል። ከዚያም በላይ አሁን ያለነው ሰዎች መጪውን ትውልድ በማሰብ ለልጆቻችን የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር ሃላፊነት እንዳለብን መዘንጋት የለበትም።

ስለዚህ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በመሐከላችን ያሉ ጊዜያዊ ልዩነቶች እንደሚጎዱን ማወቅና እርስበርሳችን ተዋደድንና ተፋቅረን ተከባብረን ሁላችንም አንድነት ፈጥረን ማኅበራችን የሚያስፈልገውን ኅብረት እንድንፈጥርና ሁልጊዜም ቢሆን ለአንድነታችን በቆርቅጥነት ለወደፊቱ እንድንሠራ አበክሬ እጠይቃችኋለሁ።

በድጋሚ «ኅብረታችን የጥንካሬአችን መሠረት ነው።»

እግዜር ይስጥልኝ። አመሰግናለሁ።